# የማጠናከሪያ ክትባት ከ mRNA ክትባት ጋር (Pfizer/BioNTech, Moderna)

**የ mRNA ክትባቶች ሆስፒታል ውስጥ መተኛትን የሚያስከትሉ ከባድ የኮቪድ-19 ክትባቶችን በጥሩ ሁኔታ ይከላከላሉ። እንደ ግለሰቡ ዕድሜና የልውጥ ዝርያው ዓይነት፣ ክትባቱ የሚፈጥረው የመከላከል አቅም በጊዜ ሂደት ሊቀንስ ይችላል። መጠነኛ የሆኑ በሽታዎችን እና የቫይረሱን ስርጭት ለመከላከል የሚያስችል አቅም በሁሉም ሰው ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ ይቀንሳል። እንደ ልውጥ ዝርያው ዓይነትም ይህ ሁኔታ ይበልጥ ወይም ባነሰ ፍጥነት ሊከሰት ይችላል። በዚህም ምክንያት፣ ዕድሜው 12 ዓመት የሞላው ማንኛውም ሰው የማጠናከሪያ ክትባቱን እንዲወስድ እንመክራለን።**

## የማጠናከሪያ ክትባቱ ዓላማ ምንድን ነው?

የማጠናከሪያ ክትባቱ የበሽታ መከላከያ ስርዓት ፖቶጂንን እንዲያስታውስ ያደርገዋል። ይህም ክትባት የሚያስገኘውን የመከላከል አቅም ወደነበረበት የሚመልስና የሚያራዝም ነው።

## የማጠናከሪያ ክትባት እንዲወስዱ የሚመከሩት እነማን ናቸው?

ዕድሜያቸው 12 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች የማጠናከሪያ ክትባት ይመከራል።

- 65 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸው ሰዎች
  ለእነዚህ ግለሰቦች የማጠነካሪያ ክትባቱ በዋነኛነት የሚመከረው በሆስፒታል ተኝቶ መታከምን ከሚጠይቅ ኮቪድ 19 የተሻለ ጥበቃ ለመስጠት ነው። በተለይም ደግሞ ለሚከተሉት ሰዎች ይመከራል፡-
  - ዕድሜያቸው 75 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች፤
  - ዕድሜያቸው 65 ዓመትና ከዚያ በላይ ሆኖ ለከባድ የኮቪድ-19 በሽታ ከፍተኛ ተጋላጭ[1] የሚያደርግ ስር ሰደድ በሽታ ላለባቸው ሰዎች፤
  - በእንክብካቤ ማዕከላት፣ በመኖሪያ ቦታ የእንክብካቤ ቦታዎችና ለአረጋውያን በተዘጋጁ የእንክብካቤ ማዕከላት ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎችና እንክብካቤ የሚያገኙ ሰዎች።
- ዕድሜያቸው ከ16 እስከ 64 ዓመት የሆናቸው ሰዎች
  ዕድሜያቸው ከ65 ዓመት በታች ለሆናቸው ሰዎች፣ የማጠናከሪያ ክትባቱ ከኢንፌክሽን፣ በተደጋጋሚ ከሚከሰት መጠነኛ ሕመምና አልፎ አልፎ ከሚከሰት ከባድ ሕመም እና ይህም ከሚያስከትላቸው ውጤቶች (ለምሳሌ፡- የኮቪድ 19 ዘላቂ ጉዳቶችና ስራ ለመስራት አለመቻል)። የቫይረሱን ስርጭት በጊዜያዊነት ለመቀነስም ያግዛል። ምክረ ሃሳቡ በተለይ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው ሰዎች የሚከተሉት ናቸው፡-
  - ዕድሜያቸው ከ65 ዓመት በታች ሆኖ የኮቪድ-19 በሽታ ከፍተኛ ተጋላጭ የሚያደርግ ስር ሰደድ በሽታ ላለባቸው ሰዎች፤
  - በእንክብካቤ ማዕከላት፣ በመኖሪያ ቦታ የእንክብካቤ ቦታዎችና ለአረጋውያን በተዘጋጁ የእንክብካቤ ማዕከላት ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎችና እንክብካቤ የሚያገኙ ሰዎች።
  - ከታካሚዎች ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው የጤና እንክብካቤ ሰራተኞችና ለተለየ ስጋት ተጋላጭ የሆኑ ተንከባካቢዎች።

  እርግዝናቸው 2ኛ መንፈቅ ላይ የደረሱ ነፍሰ ጡር ሴቶችና ጡት የሚያጠቡ እናቶችም የማጠናከሪያ ክትባቱን እንዲከተቡ ይመከራል።
- ዕድሜያቸው ከ12 እስከ 15 ዓመት የሆናቸው ጎረምሶች
  ለእነዚህ ግለሰቦች፣ የማጠናከሪያ ክትባቱ የሚመከረው ኢንፌክሽን እና መጠነኛ ሕመምን የመከላከል አቅማቸውን ለመጨመርና የቅርብ ንክኪ ለሚኖራቸው ሰዎች (የቤተሰብ አባላት) በሽታውን የማሰራጨት ዕድላቸውን ለመቀነስ ከፈለጉ ነው።

## የማጠናከሪያ ክትባት መጠሰት ያለበት መቼ ነው?

መደበኛ የ mRNA ክትባት ሙሉ በሙሉ ከተወሰደ ከ4 ወራት በኋላ ክትባት መውሰድ ይመከራል። የተሟላ መሰረታዊ በሽታ የመከላከል አቅም የሚፈጠረው

- የ mRNA ክትባት በሁለት ዙር ከተሰጠ በኋላ፤ ወይም
- በኮሮና ቫይረስ ኢንፌክሽን መያዙ ከተረጋገጠ እና ቢያንስ ከ4 ሳምንት በኋላ አንድ የ mRNA ክትባት ከተሰጠ (ቅደም ተከተሉ ምንም ቢሆን)።

በ mRNA ክትባት የተሟላ በሽታ የመከላከል ስርዓት ከተፈጠረ በኋላ በኮሮና ቫይረስ ከተጠቁ፣ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተፈጻሚ ናቸው፡

- በበሽታው የተያዙት መሰረታዊ በሽታ የመከላከል ስርዓት በተፈጠረ በ4 ወራት ውስጥ ከሆነ፣ ከኢንፌክሽኑ አራትወራት በኋላ የማጠናከሪያ ክትባት መውሰድ ይመከራል።
- መሰረታዊ ክትባት ከተወሰደ ከ4 ወራት በኋላ ኢንፌክሽነ ከተከሰተ፣ የማጠናከሪያ ክትባት በዚህ ጊዜ አስፈላጊ አይሆንም።

ሙሉውን የመጀመሪያ ክትባት ከወሰዱ በኋላ በ4 ወራት ውስጥ በቫይረሱ ለተያዙ ሰዎች የማጠናከሪያ ክትባት መውሰድ አይመከርም።

## ለማጠናከሪያ ክትባት የሚያገለግለው ክትባትና የመድሃኒት መጠን የትኛው ነው?

በመሰረቱ፣ የሚቻል ከሆነ በሽታ ለመከላከል የተሰጠው የክትባት ዓይነት ለማጠናከሪያ ክትባትም መሰጠት አለበት። ይህ የማይቻል ከሆነ፣ ሌላ የ mRNA ክትባት መጠቀም ይቻላል። መጀመሪያ የተወሰዱት የ mRNA ክትባቶች የተለያዩ ከሆኑ፣ ማጠናከሪያው ከሁለቱ ክትባቶች በአንዱ ሊሰጥ ይችላል።

ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 29 ዓመት ለሆናቸው ሰዎች እንደ ማጠናከሪያ ቢሰጥ የሚመከረው Pfizer/BioNTech ክትባት ነው። አጠቃላይ ምክረ ሃሳቡም ዕድሜያቸው ከ 12 እስከ 17 ዓመት ለሆናቸው ሰዎች የ Pfizer/BioNTech ክትባት እንደ ማጠናከሪያ እንዲሰጥ ነው።

ለ Pfizer/BioNTech ክትባት፣ ለማጠናከሪያ የሚሰጠው መጠን ከመደበኛው የክትባት መጠን ጋር ተመሳሳይ ነው። ለሞደርና (Moderna) ክትባት፣ ለማጠናከሪያ ክትባቱ የሚሰጠው መጠን ግማሽ ነው።

## ክትባቱን መውሰድ የምችለው የት ነው?

ክትባቱን የመስጠት ሃላፊነት የወረዳዎች ነው። የት ተመዝገበው መከተብ እንደሚችሉ ለማወቅ የወረዳዎን ድረ ገጽ ወይም የመረጃ መስመር ይመልከቱ (www.foph-coronavirus.ch/cantons)።ወይምዶክተርዎን፣ ፋርማሲስትዎን ወይም ፋርማሲዎን ያነጋግሩ።

**የቀረው መረጃ ለማጠናከሪያ ክትባትና ለመደበኛ ክትባት ተመሳሳይ ሲሆን፣ በዚህ የመረጃ ቅጽ ላይ ይገኛል፡ *«የኮቪድ-19 ክትባት የሆኑትን mRNA ክትባት የተመለከተ አጠቃላይ መረጃ»*.**

---

[1] ሰንጠረዥ 2፣ ገጽ 11 የ mRNA ክትባት ምክረ ሃሳብ፡ *«ሥር በሰደደ በሽታዎች ምክንያት ከፍተኛ ተጋላጭነት ላላቸው ግለሰቦች የበሽታ ፍቺዎች» (በጀርመን ቋንቋ)*